የመንገድ ደህንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት
Road Safety & Insurance Fund Service

# የብስክሌት ትራንስፖርት የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራርን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር…/ 2017 ዓ.ም

ሐምሌ/ 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## መግቢያ

በመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ዘርፍ ውስጥ ከሚጠቀሱ የትራንስፖርት ዓይነቶች ውስጥ አንዱ የሞተር አልባ ትራንስፖርት አገልግሎት ሲሆን በዋናነት የብስክሌት ትራንስፖርት በሀገራችን ከተሞች የትራፊክ መጨናነቅን የሚቀንስ፣ አስተማማኝና ቀጣይነት ያለው፣ በቀላሉና በአነስተኛ ዋጋ አገልግሎቱን ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል ከመሆኑም ባሻገር ለአየር ንብረት ብክለት ምክንያት የሆነውን ከባለሞተር ተሽከርካሪዎች የሚወጣውን የካርቦን ልቀት ለመቀነስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

በመሆኑም የብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጡን ተደራሽ፣ ለአጠቃቀም ምቹ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ለማድረግ የሚያግዝ የአሰራር መመሪያ እና ስርዓት በመዘርጋት የአገልግሎት አሰጣጡን በአግባቡ መምራትና መቆጣጠር በሚያስችል ደረጃ ሕግን መሠረት ያደረገ መመሪያ መኖሩ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

በዚሁ መሰረት የብስክሌት አገልግሎት አሰጣጥ እና አሰራር መመሪያ ማዘጋጀት በማስፈለጉ ሚኒስቴሩ በመንገድ ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 1274/2014 አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀፅ 15 መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የብስክሌት ትራንስፖርት የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራርን ለመወሰን መመሪያ" ቁጥር ---- / 2017 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል"፡፡

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ዉስጥ፡

1) **"ሚኒስቴር"** ማለት የትራንስፖርት እና ሎጅስትክስ ሚኒስቴር ማለት ነው፡፡
2) **"ክልል"** ማለት በህገ መንግስቱ አንቀጽ 47 መሰረት የተቋቋመ ክልል ነው፡፡
3) **"የከተማ አስተዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ እና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደር ነው፡፡
4) **"አገልግሎት"** ማለት የመንገድ ደህንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት ማለት ነዉ፡፡
5) **‹‹የትራንስፖርት ቢሮ››** ማለት ትራንስፖርትን ለመምራት ስልጣን የተሰጠው የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት የሚመራ አካል ነው፡፡
6) **"ብስክሌት"** ማለት በተለየለት መንገድ ላይ ተጠቃሚው ከቦታ ወደ ቦታ ለመንቀሳቀስ የሚጠቀም በፔዳል እና በኤለክትርክ ቻርጅ የሚሰራ ተሽከርካሪ ነው፡፡
7) **"የብቃት ማረጋገጫ ሰርትፊከት"** ማለት በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ የሚሳተፉ አገልግሎት ሰጭ ማህበራት ወይም ግለሰብ ማሟላት ያለባቸውን መስፈርት ካሟሉ በኃላ ብቁ መሆናቸውን በማረጋገጥ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፡፡
8) **"ማህበር"** ማለት የተለያዩ ሰዎች በመመሪያው መሰረት በመደራጀት የብስክሌት አገልግሎት ለመስጠት የሚሰማሩ አካላት ማለት ነው፡፡
9) **"ፓርኪንግ"** የብስክሌት ተጠቃሚዎች ብስክሌቱን ከተጠቀሙ ቦኃላ በጊዜያዊነት ብስክሌቶችን የሚያቆሙበት ቦታ ነው፡፡
10) **"ደንብ"** ማለት የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ለመቆጣጠር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር …../2016 ማለት ነው፡፡

## 3. ዓላማ

በመላ ሀገሪቱ ለብስክሌት ትራንስፖርት በተዘጋጁ መስመሮች ላይ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት የተቀናጀ እና የተሳለጠ የብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት በመስጠት የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ነው፡፡

## 4. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ መንገዶች ላይ የብስክሌት ትራንስፖርት ተጠቃሚዎች እና አገልግሎት ሰጪ ማህበራት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የብስክሌት አገልግሎት ሰጪ ማህበራት እና ግለሰቦች ፍቃድ አሰጣጥ

5. በብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ለመሰማራት ማህበራት ማሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፡-

    1. በስራው ላይ ለመሰማራት ፍቃደኛ መሆናቸውን የጽሑፍ ማመልከቻ ለፍቃድ ሰጭው አካል ማቅረብ፤
    2. በሚመለከተው አካል የፀደቀ የማህበሩ የመመስረቻ ጽሑፍ እና የመተዳደሪያ ደንብ ሰነዶችን የማቅረብ፤
    3. በአንድ ማህበር መደራጀት የሚችለው የሰው ብዛት ከ10 እስከ 20 የሆነ እና ከእነዚህ ውስጥ ሰብሳቢ፣ ጸሃፊ እና ገንዘብ ያዥ በመምረጥ የተስማሙበትን ሰነድ ማቅረብ አለባቸው፡፡
    4. በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ ለመሳተፍ የሚፈልገዉ ማህበር የራሱ ብስክሌት ቢኖረው ይመረጣል፡፡ ሆኖም ማህበሩ ፈቃደኛ ሆኖ የራሱን ብስክሌት ማቅረብ ካልቻለ በመመሪያው መሰረት ከመንግስት በመረከብ መስራት ይችላል፡፡
    5. በተለየው የብስክሌት መስመር ላይ እስከ 5 ማህበራት ሊመደቡ ይችላሉ፡፡
    6. ከመንግስት ለሚቀርቡ ብስክሌቶች በቂ ዋስትና ማቅረብ የሚችል፤

6. በብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ለመሰማራት ግለሰቦች ማሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፡-

1. በአገልግሎት አሰጣጡ ዙሪያ በሚወጣው አሰራር እና መመሪያ መሰረት አገልግሎት ለመስጠት ፈቃደኛ መሆኑን ለሚመለከተው አካል ማመልከቻ በማቅረብ በፎርማው ማረጋገጥ አለበት፤
2. ስራውን ለመጀመር ያለውን የብስክሌት ቁጥር የማሳወቅ ሀላፊነት አለበት፡፡

## 7. የፍቃድ አሰጣጥ ሁኔታ

በብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት መሰማራት የሚፈልጉ ማንኛውም ማህበር ወይም ግለሰቦች የአገልግሎት ሰጭ ማህበራት ወይም ግለሰቦች ፈቃድ ለመውሰድ በአንቀጽ 5 ንኡስ አንቀጽ 1 - 6 የተቀመጠውን መስፈርት በማሟላት ከትራንስፖርት ቢሮ የአገልግሎት አሰጣጥ ፈቃድ ማግኘት ይችላሉ፤

## 8. የብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ማህበራት ወይም ግለሰቦች እና ተጠቃሚዎች መብት እና ግዴታ

**1. የብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ማህበራት ወይም ግለሰቦች መብት**

1) ማንኛውም አገልግሎት ሰጭ ማህበር ወይም ግለሰብ በአንቀጽ 5 ንኡስ አንቀጽ 1 - 6 የተቀመጡትን መስፈርቶችን በሚማላት ፈቃድ ካገኙ በመመሪያው መሠረት ሥራዉን የመስራት፣
2) በስራቸው ላይ ለሚያጋጥማቸው የተለያዩ ችግሮች ከመንግስት አስፈላጊውን ህጋዊ ድጋፍ የማግኘት፤
3) በታሪፉ መሰረት ያከራየውን ብስክሌት የኪራይ ክፍያ የማግኘት፤

**2. ግዴታ፡**

1) ተግባራዊ እየሆነ ያለውን የብስክሌት ትራንስፖርት አሰራር መመሪያ የማክበር፤ የመተግበር፤ ተገቢውን ድጋፍ የማድረግ፤
2) በሚመለከተው አካል በተቀመጠው የታሪፍ ተመን መሰረት የብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት የመስጠት፤
3) በመንግስት የሚቀርብለትን ብስክሌቶች በአግባቡ ለመያዝ እና ለማስተዳደር ከሚመለከተው አካል በተዘጋጀው የስምምነት ሰነድ ላይ ዋስ በማቅረብ ፈርሞ የመረከብ፤
4) ማንኛውም ማህበር የብስክሌት አገልግሎት መስጠቱን ለማቋረጥ ሲፈልግ አንድ ወር ባላነሰ ጊዜ ውስጥ ለሚመለከተው አካል የማሳወቅ፡፡
5) የብስክሌቶቹን ቴክኒካዊ ብቃት የመጠበቅ፤ መለዋወጫዎችን የማዘጋጀት፣ የማስጠገን እና በአግባቡ ጽዳቱን የመጠበቅ፣

6) አገልግሎት ለሚሰጡአቸዉ ብስክሌቶች ከሚመለከተው አካል የተሰጠ ሕጋዊ የሆነ መለያ ቁጥር የመለጠፍ፤
7) የብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት በሚሰጥበት ወይም በሚጠቀምበት ጊዜ አደጋ ሲያጋጥም ተጎጂው በፍጥነት የህክምና እርዳታ እንዲያገኝ የማድረግ፤
8) የብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎቱ ውጤታማ እንዲሆን ከሚመለከታቸው መንግስታዊ ከሆኑ አካላት ጋር ተቀናጅቶ የመሥራት፤
9) የማህበራቱ ወይም የአገልግሎት ሰጭ ግለሰቦች ለአገልግሎት አሰጣጡ አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን (የሰው ሃይሉን፤ ዩኒፎርም፤ ባጅ፤ መቀያየሪያ ዕቃዎች) እንዲሟሉ የማድረግ፤
10) የብስክሌቶችን ቀለም የሚመለከተው አካል በወሰነው መሠረት የማስቀባት፣ የማሳደስ፤
11) ከመንግስት ተረክበው አገልግሎት እየሰጠበት ያለውን ብስክሌቶች ለሌላ አገልግሎት አለማዋል፤

## 9. የብስክሌት ተጠቃሚው ህብረተሰብ መብት እና ግዴታዎች፡

### ሀ) መብቶች

ማንኛውም የብስክሌት ትራንስፖርት ተጠቃሚ ህብረተሰብ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡፡

1) የብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት የማግኘት፤
2) የአገልግሎት ክፍያ ዋጋ /ታሪፍ/ መረጃ የማግኘትና የማወቅ፤
3) ለከፈለበት የአገልግሎት ክፍያ ደረሰኝ የመቀበል፤

### ለ. ግዴታዎች

ማንኛውም የብስክሌት ትራንስፖርት ተጠቃሚ ህብረተሰብ የሚከተሉት ግዴታዎች አሉት፡፡

1) ለመጠቀም የተረከቡትን ብስክሌት ከተጠቀሙ ወይም አገልግሎቱን ካገኙ በኃላ በጉዞው መጨረሻ ላይ አቁመው እንዲሄዱ በተመቻቸበት ቦታ ላይ በአግባቡ አቁመው የመሄድ፣
2) ለመሄድ የሚፈልገዉን ርቀት ለአገልግሎት ሰጭዎቹ የማሳወቅ፤
3) ለተጠቀመው አገልግሎት ተገቢውን ክፍያ የመፈፀም፤
4) ያለአግባብ በማሽከርከር ለሚያደርሷቸው የሰው እና የንብረት ጉዳቶች ተጠያቂ የመሆን እና በዚህ ምክንያት የሚወጣውንም ወጪ የመክፈል፤
5) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 4 ላይ የተቀመጠውን የጉዳት መጠን የሚወሰነው በሚመለከተው አካል እና የጤና ባለሙያ ይሆናል፡፡
6) ብስክሌቱን ለመጠቀም ሲረከቡ ለአጠቃቀሙ በተቀመጠው መመሪያ መሰረት ተግባራዊ የማድረግ፤

## 10.የብስክሌት አገልግሎት ዋጋ /ታሪፍ/ በተመለከተ

1. የብስክሌት አገልግሎት ታሪፍ የሚወጣው በሚመለከተው አካል ሆኖ በበላይ አመራር ሲፀድቅ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

### ክፍል ሦብት

### የተለያዩ አካላት ኃላፊነት

## 11. የሚኒስቴሩ ኃላፊነት፡

1) የብስክሌት ትራንስፖርት የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራርን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ያፀድቃል፡
2) የብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጡ በመመሪያው እና አሰራሩ መሠረት መፈፀሙን ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ክፍተቶችን በመለየት የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡
3) የብስክሌት የኪራይ እና በጋራ የመጠቀም አገልግሎት ለማሳደግ የተዘረጋው አሰራር ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
4) በብስክሌት አጠቃቀም ዙሪያ የሚታዩ ችግሮችን በመሠረታዊነት ለመፍታት የሚያስችሉ ጥናቶችን ያከናውናል፤ ይተገብራል፤
5) የአገልግሎት አሰጣጡ እስከ ክልል ከተሞች ድረስ መስፋፋት እንዳለበት ሁኔታዎችን ለሌሎች ከተሞቹ እንዲመቻች ያደርጋል፡፡
6) የብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የታዩ ምርጥ ተሞክሮዎችን ይቀምራል፤ ተሞክሮቹ አገራዊ ፋይዳ በሚሰጡበት አግባብ ተቃኝተው የሚተገበሩበትን ሥርዓት ይነድፋል፤ ያስተገብራል፡፡
7) የብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት ዘርፉ የሚያድግበትን ሁኔታ ከሌሎች መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር በመሆን ፈንድ በማፈላለግ ለተግባራዊነቱ በቅንጅት ይሠራል፡፡

## 12. የአገልግሎቱ ኃላፊነት፡

1. የመንገድ ትራፊክን በማሳለጥ መንገዶች ለብስክሌት ተጠቃሚዎች ስጋት የማይፈጥሩ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡
2. ከመንገድ ትራፊክ ደህንነት አንጻር ማንኛዉም ብስክሌት ሊያሟላ የሚገባዉን የደህንነት መስፈርት በየጊዜዉ ጥናት በማድረግ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
3. ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመተባበር የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ሥልጠናዎችን ለብስክሌት ተጠቃሚዎች እና አገልግሎት ሰጪ ማህበራት እና ግለሰቦች ይሰጣል፤

4. የብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት ዘርፉ የሚያድግበትን ሁኔታ ከሌሎች መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር በመሆን ፈንድ በማፈላለግ ስራ ላይ ያውላል፡፡

---

## 13. የትራንስፖርት ቢሮ ኃላፊነት፡

1) የብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት የሚመራበትን አሰራር እና መመሪያ ተግባራዊ ያደርጋል፤ ለአገልግሎቱ አስፈላጊውን ግብአት ያሟላል፤
2) የብስክሌት ትራንስፖርት አስተዳደር ሥራ በበላይነት ይመራል፤ ይቆጣጠራል፤ ለአገልግሎቱ መሳለጥ የሚያግዝ ስልት ይቀይሳል፤ ይተገብራል፤
3) ከማህበራት የሚገኘውን ማስረጃ መሰረት በማድረግ የብስክሌት ማከራያ ታሪፍ ያወጣል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፡፡
4) የብስክሌት አገልግሎት ሰጪ ግለሰቦች ወይም ማህበራትን ይመዘግባል፤ አገልግሎት አሰጣጡን ይቆጣጠራል፤ መረጃዎችን በመሰብሰብ ያደራጃል፡፡
5) በብስክሌት አገልግሎቱ ውስጥ የግሉ ዘርፍ እንዲሳተፍ የሚያበረታታ ሥርዓት ይዘረጋል፤
6) የብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ማህበራት ወይም ግለሰቦች የሚሰሩበትን የአገልግሎት ታሪፍ ያወጣል፤ ተግባራዊነቱን ይቆጣጠራል ፡፡
7) ለብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ማህበራት እና ግለሰቦች በትራንስፖርት ሕጎች፤ በብስክሌት አጠቃቀም መሰረታዊ መርሆዎች፣ መመሪያዎች እና በሥነ-ምግባር ዙሪያ ሥልጠና እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡
8) የብስክሌት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚሰማሩትን ፈቃደኛ የሆኑ ግለሰቦች እና ማህበራት የሚተዳደሩበት ዉል ግልጽ በሆነ መልኩ ያዘጋጃል ፣ እንደየአስፈላጊነቱ በየአመቱ ያድሳል፤
9) በብስክሌት መንገድ ላይ በግልም ሆነ ከማህበራት በኪራይ ለሚጠቀሙ ብስክሌተኞች ሌሎች አካላት ችግር እንዳይፈጥሩ ከሚመለከተው አካል ፣ ከትራፊክ ፖሊስ፤ ከደንብ ማስከበር እና ከሌሎች ሕጋዊ አካላት ጋር በመተባበር ይሠራል፡፡
10) ለብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት መስጫ የሚሆን የተለየ መንገድ እንዲዘጋጅ ይሰራል፤

11) በብስክሌት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ለመሰማራት ፍላጎት ላላቸው ማህበራት ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ የብስክሌት መለያ ቁጥር በማዘጋጀት ለብስክሌት ባለቤቶች/ ማህበራት ያሰራጫል/ይሰጣል፡፡

12) የትራፊክ አመራርና አስተዳደር ሥራ በበላይነት ይመራል፤ ይቆጣጠራል፤ ለአገልግሎቱ መሳለጥ የሚያግዝ ስልት ይቀይሳል፤ ይተገብራል፡፡

13) በብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጡ ዙሪያ የሚታዩ ህገ ወጥ ተግባራትን ይቆጣጠራል፣ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፡፡

14) የብስክሌት ተጠቃሚ ደህንነትን ለማሻሻልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ዘመናዊ የቴክኖሎጂ ሥርዓት ይዘረጋል፤ የመረጃ ሥርዓቱን በመጠቀም የትራፊክ ደህንነቱንና ፍሰቱን ይከታተላል፤ መረጃዎችን ያደራጃል፤ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፡፡

15) የብስክሌት ስርቆትን እና አገልግሎቱን ለመቆጣጠር የሚያስችል የተለያዩ የቴክኖሎጂ ተሞክሮዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

16) ለብስክሌት አገልግሎት የተለዩ መንገዶች (መስመሮች) የሚያስፈልጉ የትራፊክ ምልክቶች እና ማመላከቻዎች፣ የመንገድ ላይ ቅቦችን ይተገብራል፤ ያስተዳድራል፡፡

17) በብስክሌት አጠቃቀም ዙሪያ ያሉትን መረጃዎችን ይሰበስባል፤ያቀናጃል፤ እንደ አስፈላጊነቱ በግብዓትነት ይጠቀማል፡፡

18) የብስክሌት ማቆሚያ ፓርኪንግ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ በአተገባበሩም ላይ የሚታዩትን ክፍተቶችን በመለየት እንዲፈታ ያደርጋል፡፡

19) የብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጡን ለማስጀመር በሚደረገው ተግባራት ላይ በመሳተፍ አስፈላጊውን ሙያዊ እና ህጋዊ ድጋፍ ይሰጣል፤

20) ለብስክሌት አገልግሎት የሚውሉ የብስክሌቶችን ቀለም ይወስናል፤እንዲቀቡም ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤

21) ለብስክሌት ተጠቃሚዎች እና ማህበራት በመንገድ ደህንነት እና ፍሰቱ ላይ ግንዛቤ ይፈጥራል፤

## 14. የክልል እና የፌደራል መንገዶች ባለስልጣን አስተዳደር ኃላፊነት፡

1. ለብስክሌት አገልግሎት የሚውሉ መንገዶች የዲዛይን ስራ ላይ ሙያዊ ድጋፍ ያደርጋል፡፡
2. የብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡበትን የመንገድ መሰረተ ልማት ከሚመለከታቸው የመንግስት ተቋማት ጋር በመቀናጀት እንደ ከተማው አስተዳደሩ ተጨባጭ ሁኔታ ይገነባል፣ ይጠግናል፡፡

## 15. የክልል መሬት ልማት እና አስተዳደር ቢሮ ኃላፊነት፡

ለብስክሌት መሰረተ ልማት (መንገድ እና ማቆሚያ ፓርክንግ) ግንባታ የሚዉል ቦታ ይፈቅዳል፤

**16.የክልል ፕላን ልማት ኮሚሽን ኃላፊነት፡**

የብስክሌት ማስፋፊያ እቅድ ከከተማው ማስተር ፕላን ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

**17.የሥራ፣ ኢንተርፕራይዝ እና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ኃላፊነት፡**

በብስክሌት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ለመሰማራት ፍላጎት ያላቸውን ማህበራት ያደራጃል ፣ማስረጃ ይሰጣል፡፡

**ክፍል አራት**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

**18. ስለ አገልግሎት ክፍያ**

የብስክሌት ትራንስፖርት የአገልግሎት ኦፕሬተርነት ፈቃድ ለማውጣት ወይም ለማሳደስ በእያንዳንዱ ብስክሌት የሚከፈለውን የአገልግሎት ክፍያ የክልሉ ትራንስፖርት ቢሮ በሚያወጣው የታሪፍ መመሪያ ይወሰናል፡፡

**19.የመተባበር ግዴታ**

1. ማንኛውም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ተቋማት ይህን መመሪያ ለማስፈፀም ስልጣን ከተሰጣቸው አካላት ጋር የመተባበር እና ሚናቸውን የመወጣት ግዴታ አለባቸው፡፡
2. ይህን መመሪያ የጣሰ ወይም እንዳይፈፀም ያሰናከለ አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**20.የመተግበር ግዴታ**

1. ማንኛውም ሰው ለአሽከርካሪው ተብሎ በብስክሌቱ ላይ በተዘጋጀው መቀመጫ ላይ ተመቻችቶ ሳይቀመጥ ማንኛውንም ብስክሌት መንዳት የተከለከለ ነው፡፡
2. ማንኛውም ብስክሌት አሽከርካሪ ብስክሌቱን በሚነዳበት ጊዜ የብስክሌቱን መሪ በእጆቹ ሳይዝ በእግሮቹም የብስክሌቱን ማሽከርካሪያ ሳይቆነጥጥ መንዳት የተከለከለ ነው፡፡
3. ማንኛውም ሰው ብስክሌት በሚነዳበት ጊዜ በማንኛውም አኳሃን በመጓዝ ላይ ያለ ሌላ ተሽከርካሪ መያዝ ወይም ራሱ ወይም ብስክሌቱ በሌላ ተሽከርካሪ እንዲጎተት ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

4. የብስክሌት አሽከርካሪዎች ቅደም ተከተል መስመርን ይዘው መንዳት አለባቸው፡፡ ሆኖም ለሌላ ትራፊክ እንቅፋት የማይሆኑ ከሆኑ ሁለት ብስክሌት አሽከርካሪዎች ብቻ ጎን ለጎን ሆነው ለመንዳት ይችላሉ፡፡
5. ማንኛውም ማህበር ወይም ግለሰብ ፍሬን የሌለውን ብስክሌት ለአገልግሎት መስጫ ማቅረብ የተከለከለ ነው፡፡
6. ማንኛውም ሰው የማስጠንቀቂያ ደወልና የተሟላ ፍሬን የሌለው ብስክሌት መንዳት የተከለከለ ነው፡፡
7. ማንኛውም ብስክሌት አሽከርካሪ የአደጋ መከላከያ ቆብ (ሄልሜት) ማድረግ አለበት፡፡

**(395 የመጣ ስለሆነ ይውጣ)**

### 21.የዲሲፕሊን ጥፋቶች፣ የቅጣት ደረጃዎች እና የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ሥርዓት

### 22.ደረጃ አንድ የጥፋት ዓይነቶች ቅጣት

1) የተሰጠውን ፈቃድ በወቅቱ አለማሳደስ፤
2) ከተፈለገው አላማ ውጪ መሥራት፤
3) በብስክሌቱም ሆነ በተጠቃሚው ላይ አደጋ ሲደርስ ወዲያውኑ ለትራንስፖርት ቢሮ አለማሳወቅ፤
4) ቢሮው ባወጣው ታሪፍ መሠረት አለመሥራት፤
5) በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 4 ከተጠቀሱት ጥፋቶች አንዱን የፈፀመ ማህበር ወይም አገልግሎት ሰጭ ግለሰብ ብር 100.00 (አንድ መቶ ብር) ይቀጣል፡፡
6) ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ጥፋቶች መካከል በአንድ ጊዜ ከአንድ በላይ ጥፋት የፈፀመ ማህበር ወይም አገልግሎት ሰጭ ግለሰብ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 የተመለከተው ቅጣት በእያንዳንዱ ጥፋት ልክ ተባዝቶ ይቀጣል፡፡

### 23.ደረጃ ሁለት የጥፋት ዓይነትና ቅጣት

1) በስራ ላይ እያለ አግባብነት ባላቸው የቁጥጥር ሠራተኞች ወይም ሌሎች ሕጋዊ አካላት ማንኛውንም ዓይነት መረጃ ሲጠየቅ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን ወይም አለመተባበር፤
2) ማህበሩ ወይም አገልግሎት ሰጭ ግለሰብ መስመሩን መሸፈን ወይም አገልግሎት መስጠት ሲያቋርጥ ለክልሉ ትራንስፖርት ቢሮ አለማሳወቅ፤

3) በደረጃ አንድ የጥፋት እርከን የተዘረዘሩትን ጥፋቶች ለሁለተኛ ጊዜ የፈፀመና በሪከርድ የተያዘበት ማህበር ወይም አገልግሎት ሰጭ ግለሰብ በደረጃ ሁለት ቅጣት 200 ብር ይቀጣል፡፡

4) በደረጃ አንድ እና ደረጃ ሁለት የተቀመጡትን ጥፋቶች አጥፍቶ ከተቀጣ በኃላ ካልተስተካከለ እና ተጨማሪ ጥፋት ካጠፋ ፈቃዳቸው እንድሰረዝ ይደረጋል፡፡

## 24. ስለ ቅሬታ አቀራረብ እና አፈታት ሥርዓት

1) ማንኛውም ቅሬታ ያደረበት ማህበር ወይም ግለሰብ ቅሬታውን በተፈጠረ በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ ለክልሉ ትራንስፖርት ቢሮ ለሚመለከተው ክፍል ማቅረብ ይችላል፡፡
2) የክልሉ ትራንስፖርት ቢሮ የሚመለከተው ክፍል ቅሬታው በቀረበ በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ ለቅሬታ አቅራቢው በጽሑፍ ውሳኔውን ማሳወቅ አለበት፡፡
3) የክልሉ ትራንስፖርት ቢሮ የሚመለከተው ክፍል በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማህበር ወይም ግለሰብ ውሳኔው በተሰጠ በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለክልሉ ትራንስፖርት ቢሮ የበላይ ኃላፊ ያቀርባል፡፡

የክልሉ ትራንስፖርት ቢሮ የበላይ ኃላፊ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻው አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሆናል፡፡

## 25. ተፈጻሚነት የማይኖራቸዉ ህጎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛዉም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረዉም፡፡

## 26. መመሪያዉን ስለማሻሻል

አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሚኒስቴሩ ይህን መመሪያ ሊያሻሽለዉ ይችላል፡፡

## 27. መመሪያዉ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ …… ቀን /2017 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

ዶ/ር ዓለሙ ስሜ

የትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ ሚኒስቴር

ሚኒስትር